# ያልተገላበጠ

ቀን ቀንን ሲወልድ ፤ እድሜዬ ሲጨምር

እኔስ አንድ ቦታ ፤ እንዴት ቆሜ ልቅር ።

ሲነጋ ኢሕአፓ ፤ ሲመሻሽ ወያኔ

ልገላበጥ እንጂ ፤ ካልተመቸው ጎኔ ።

ወይ ፓርቲ ማቋቋም ፤ የራሴ የግሌ

ወይ ቅንጅት ፈጥሮ ፤ ማፍረስ እንዳመሌ ።

ተሰድጄም ብሄድ ፤ ተራራ ብወጣ

አንድ ቦታ አልቆምም ፤ የመጣው ቢመጣ ።

ኪል ብዬ ካልሰራ ፤ ግንቦት እሆናለሁ

የልቤ እስኪሞላ ፤ እገላበጣለሁ ።

ግቤን እስክመታ ፤ ገንጣይ ቢያስወድደኝ

ሁሉን እሆናለሁ ፤ ለኔ ከተመቸኝ ።

ሰው ያሻውን ይበል ፤ አውርቶ ይቀራል

ያልተገላበጠ ፤ እንደ ቂጣ ያራል ።

ምን ያሳርረኛል ፤ ለምን እከስላለሁ

እስር ጊዜም ቢሆን ፤ እከረበታለሁ ።

እኔን ከተመቸኝ ፤ ሰው ያሻውን ያውራ

የራሴ ህልም አለኝ ፤ አይደለሁ ሸውራራ ።

ሌላው እስኪገባው ፤ ስልጡን ፖለቲካ

ማክረር አያሻኝም ፤ አይደለሁ ማስቲካ

አምልጬ እሄዳለሁ ፤ ወሬውን ሲከካ

በኦነግ ታጅቤ ፤ ወያኔን ልተካ ።

ታዛቢው ... July 23/2011

EthioLion.Com